ምዕራፍ 3፦ የማህበረሰባችን እንቅስቃሴዎች

- 3.1 ግብርና፦ የሰብል ምርትን፣ የዶሮ እርባታን፣ የንብ እርባታንና ደንን የሚያጠቃልል የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው።

3.1.1 አፈርና የሰብል አመራረት

- አፈር፦ በመሬት ገፅ ላይ የሚታይ ከጥቃቅን የድንጋይ ስብርባሪዎች፣ አፅፅዋትና ከእንስሳት ብስባሽ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ነው።

የአፈር ቀለማት

አፈር የተለያዩ ቀለማት ሲኖሩት ጥቁር ፣ ቡናማ፣ቀይና ቢጫ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የአፈር ጥቅም

- ተክሎች እንዳይወድቁ ያደርጋል።
- ለተክሎች በቂ ውሃና ንጥረ ምግቦች በኩል እንዲደርስ ያደርጋል ።
- ተክሎች ለምግብነት፣ ለገቢ ምንጭነት፣ ለአካባቢ ውበትና ለመሳሰሉት ይጠቅማል።

- የዘር መዝሪያ መደብ ለማዘጋጀት ፦ ትክክለኛ ቦታ መምረጥ

  - የመትከያ መደብ ማዘጋጀት
  - የውሃ ቦይ መስራት
  - አፈሩን ማለስለስ
  - በአፈሩ ውስጥ ማዳበሪያ መጨመር

- መደብ ማለት ከሌላው መሬት ያነሰ ወይም ከፍ ያለ የችግኝ ማብቀያ ቦታ ነው።

ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች

- ዶማ፣ አካፋ፣ ማንገዋለያ ወይም መቧጠጫ፣ ውሃ ማጠጫና መጓጓዣ(ጋሪ) ናቸው፡፡

መቆፈሪያዎች

- ዋና ዋና የመቆፈሪያ አይነቶች፦ ዶማ እና ጃምባ በመባል ይታወቃል፡፡

ተክሎችን መንከባከብ

- ተክሎችን ፦ ውሃ በማጠጣት እንዳይቀጭጩ ማሳሳት

- ማረም
- መኮትኮት
- ማዳበሪያ መጨመር
- ከተባይና ከበሽታ መከላከል በጣም አስፈላጊ ነው
- አረም የተክሎችን ምግብ የሚሻማ ነገር ነው

ተክሎችን የሚያጠቁ እንስሳት

- አንበጣ፣ አይጥ ና አዕዋፍ ችግኞችን/ተክሎችን/ በማጥቃት እንዲሞቱ ያደርጋሉ።
- የተክሎችን ጉዳት - ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመጨመር

  -ጎጂ ተባዮችንና እንስሳትን የሚመገቡ ሌሎች እንስሳት በማርባት

  - በማጠር መከላከል ይቻላል።

ዝንብ

- የትንኝ ዘር ስትሆን በቤታችንና በአካባቢያችን ትታያለች።በሰዎች ላይ ጉዳት ታደርሳለች
- የሚኖሩት በቆሻሻ ላይ ነው። እንቁላላቸውን ባልተሸፈነ ምግቦችና በእንስሳት እዳሪ ላይ ይጥላሉ።
- የዝንብ ዑደተ ህይወት - የታይፎይድ፣ ኮሌራና ትራኮማ በዝንቦች አማካኝነት የሚከሰቱ በሽታዎች ናቸው።
- እንቁላል- 1ኛ ደረጃ ዕጭ- 2ኛ ደረጃ ዕጭ -3ኛ ደረጃ ዕጭ - ሙሽሬዎች - ጉልምስ ዝንብ

የወባ ትንኝ

- የወባ ትንኝ(ሴቷ የወባ ትንኝ) በሽታን ከሰው ወደ ሰው አስተላላፊ ጎጂ ነፍሳት ናት።
- የወባ ትንኝ የሕይወት ዑደት
- እንቁላል ዕጭ ሙሽሬ ጉልምስ ትንኝ

የንብ እርባታ

- ንቦች ቀሰምን ሰብስበው ማር ይሰራሉ። እነርሱም በሶስት ይከፈላሉ።
- 1. ንግስት 2. አውራ ንቦችና 3. ሰራተኛ ንቦች ይባላሉ።

የንብ ዑደተ ህይወት

- እንቁላል - እጭ - ሙሽሬ - ጉልምስ ንብ
- ማር በዘመናዊና በባህላዊ ዘዴ ይመረታል።
- ዘመናዊ የንብ እርባታ ከባህላዊ ዘዴ የተሻለ የምርት መጠንና ጥራት ያለው ማር ለማግኘት ያስችላል።
- የእጅ ምስሪት በመጠቀም የትናንሽ እንስሳትን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች በቀላሉ ለማጥናት ይጠቀማል።